# አሸር ባሸር ፖለቲካ

## ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ የቀረበ ሀተታ

ቦጅ ቦጅ ፖለቲካ፤ ዝብርቅርቅ ፖለቲካ፤ ላፊሶ ፖለቲካ -- በጥቅሉ ፖለቲካ ጮቤ ብለን ልናቀርበው እንችላለን። በኢትዮጵያና መሰል ሀገሮች ፖለቲካ ቧልት አይደለም። የሀገርና የሕዝብን መሰረታዊ ዕጣና ሕልውና ወሳኝ ነው። ሕብረተሰቡም በተጻራሪ ሁኔታ ተከፍሎ የሚገኝበት ነው። ብሔራዊ ከበርቴ መደብ ወይም በሰርቶ አደሩና በከበርቴው መሀል መካከለኛ መድብ አለ ተብሎ ቢለፈፍም በሀገራችን ሆነ በመሰል ቦታዎች ራሱን ለባዕድ የሸጠና ሀገርን ሕዝብን የበዘበዘ ባለስልጣን ክፍል ሲኖር በሌላ በኩል ደግሞ ያለው ሰፊው ጭቁኑ ሕዝብ ነው። በሁለቱ መሀል ያለው ቅራኔ የሚታረቅ ነው ብለው የሚሰብኩ ወደዱም ጠሉም ከበዥባገሮቹ ጎን የሚመደቡ ናቸው። ይህን ማስቀደሙ የግድ የሆነው ትግልና ፖለቲካ የጡረታ ጊዜ ስራ፤ ዝና ፍለጋ ስምሪት ወይም ፖለቲካን እንደ ንግድ ወስዶ መነገድ ለማትረፍ መማር ለመለፍለፍ በሚል መሆን የለበትምና ነው።

ዳግም አሸር ባሸር ፖለቲካ ያብቃ ማለት ያስገደደን ሁኔታ አንድም የሕዝብን ሀቀኛ ትግል ወደ ድል ለመውሰድ የምንጓዝበት አቅጣጫና ስልት የተሳሳተ እየሆነ በማስቸገሩ ብቻ ሳይሆን ወያኔ በተደናገሩና ወይም ቅጥረኞቹ በሆኑት አማካይነት በአባይና ግብጽ ጉዳይ ባድሜ ቁጥር ሁለትን ሊጫወትብን እየጣረ በመሆኑም ነው። ወያኔ ሀገራዊ ጥቅምን ወይም ብሐራዊ ኢትዮጵያዊ ስሜትን መቸም ሆን መቼ ሊያንጸባርቅ የማይችል መሆኑ እየታወቀ--ባድሜን ረስተው-- ከወያኔ ጎን ቆመን አባይንም እንገድባለን፤ ግብጽንም እንዋጋለን ብለው መፎክህ የጀመሩት ክፍሎች ይህን ዓይነት አጉል ድንፋታና የወያኔ ሰለባነት ይታይባቸዋል ተብለው ያልተጠበቁ ነበሩም ጭምር ናቸው ማለት ይቻላል። ወያኔ የ1997ኡን ሁኔታ በግድያ ብቻ ሳይሆን በሰርጎ ገቦች --በተለይም ወጣት በተባለና ተቃዋሚ ነኝ ብሎ ባወናበደ ቅጥረኛው አማካይነት-- ሊያፍን ሊለውጥ መቻሉን የረሳን ይመስል ዛሬ ደግሞ ያንኑ ተመሳሳይ ሁኔታ ሊደግም ሲነሳ ዓይናቸውንም ሕሊናቸውንም ጨፍነው በጠራራ ጸሐይ አጀሃ አሞኘን የሚሉ ብቅ ብቅ ብለዋል። አንዳንዶቹ የለመደባቸው የትግል ጠላቶች መሆናቸው ጉዳቱን አይቀንሰውም ። በባድሜ 130ሺ ዜጋ አስጨርሰን ምን አገኘን? ዜሮ፤ ምንም! የወያኔ የሀሰት ወሬ ነገር ተቋም-- ስሙን ካልቀየሩት ባዶ ሶስት ይባል የነበረ

ነው --አሰብን ልንይዝ ነው ብሎ ሲለፍፍ ያመኑት ጥቂቶች አልነበሩም። የዓለም ፍርድ ቤትም ለሻዕቢያ ሲፈርድ መለስም፤ ስዩምም በረከትም ወዘተ ድል ተገኘ ብለው ሕዝብን ሊያታልሉ ሞክረው አልነበር?

ዜጎችና ተቃዋሚ ክፍሎችም ራሳቸው የሚፈለገው ጸረ ወያኔ ትብብር አለመኖሩ ቀጣይ ችግር ሆኖ መባጅቱን ያምኑበታል። ታላቁና ከባዱ ግዳጅ--ማለትም ወያኔን መጣል ማስወገድ-- እንዲቀጥል መተባበርና በጋራ መታገሉ ፍሬያማ ይሆናል ተብሏል--ነውም። ይህ በዚህ እንዳለ ግን የሕብረቱና የጋራ የተቀናጀ ትግል አያያዙ ራሱ ዝብርቅርቁ ወጥቷል። የወያኔ አገዛዝ ጠላት ነውና እንገርስሠው ሲባል አንዳንዶች የኢትዮጵያ መንግስት እያሉና የሌለውን ዴሞክራሲያዊነት አለው ብለው፤ ድንገትም አሳየ ብለው እየተፈጠሙና ማፈሪያ ደብዳቤዎችም እየጻፉለት መለማመጡን ተያይዘውታል። ወያኔን የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የሚሉም አሉ። ሌሎች ደግም ስለ ሕብረት ሆነ ሽግግር ሂደትና ይዘት ከቶም መረዳት አቅቷቸው ተያይዞ ገደልን ወደዱም ጠሉም አስፍነዋል። የሕብረት ጥረት ነጽብራቅ እኛ ብቻ ነን የሚሉ ና ያውም መሶብ የማይከፍቱ ኢምንት ስብስቦች ስንት ናቸው? ለምንስ እርስ በርስ መተባበር አቃታቸው? በተለይም የራሳቸውን አሳዛኝ ድክመት ለመሸፈን ይበጠብጠናል ያሉት ኢሕአፓ ርቋቸው ባለበት ሁኔታ? ይህ ሁሉ መልስን ጠያቂ ነው። በሀገር ቤት ሕልውና የሌላቸው ቡድኖች በባዕድ ሀገር በተለይም በአሜሪካ የእግር ኳስ ግጥሚያ ሰሞን ለሕብረት በሚል ጥሪና ስብሰባ ማድረጋቸው ራሱ ችግሩን ይጠቁማል። በሀገር ቤትም ቢሆን ያሉት በዚህ በዚያ ስብስብ ነን ቢሉም ሊተባባሩ አለመቻላቸው ምስጢር አይደለም። ለምን ይህ ሆነ ? ይህንን በ ጥሞና መመርመሩ ተገቢ ነው። ሕብረትን በሀገር ቤት በተጨባጭ ትግል ዙሪያ ወይም ክስተት አጅበን እንሞክረው የተባለው ጠቃሚነቱና መፍትሔነቱ ግልጽ ነው። ኢሕአፓ ይህን ሲል የለም ራሱም ሕልውና የለውም የሚሉቱ ደግሞ ሕልውና ካላቸው በሀገር ቤት በቃል ሳይሆን በገቢር እየታገሉ ለምንስ ማበር አቃታቸው? ሕዝብን በሌለ ሕብረት መደለል፤ ማደናገርና አጉል ተስፋ ሰጥቶ ለእንቅልፍ መጋበዝ የሚጠቅመው ወያኔን ብቻ ነው። የሌለን ታጋይ ጦር አለ፤ ብዙ ሺ ነው፤ መጣላችሁ ብሎ መዋሸትም ወያኔን አይፈታውም።

ሕብረት ተመሳሳይ አላማና ግብን ይጠይቃል-- የሁሉም የፖለቲካ መርሕ አንድ ይሁን ባይባልም። ወያኔን በሰላም እንጥላለን የሚሉትና የለም የሚቻለው በትጥቅ ነው የሚሉት

የመጀመሪያዎቹ ራሳቸውን ለአደጋ ካላጋለጡ መተባበር ይችላሉ -- ከዚህ ቀደምም ታይቷል። በሁለቱ የትግል ስልቶች መሀል ቅራኔ የሚፈጥሩት ብዙዎቹ ባለማወቅ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ለአገዛዙ ተገን ለመሆን ነው። ሕብረት ግን ወያኔ ወዳጃችን ነው በሚሉትና ስርዓቱን በሚደግፉና ይህን በሚጻረሩ መሀል መጣሩ ደግሞ ከንቱ ልፋት ነው። የኢትዮጵያ አንድነት ተጠብቆና ዴሞክራሲ ሰፍኖ እንዲገኝ እንታገላለን የሚሉትና ተገንጥለን ሌላ ሀገር እንሆናለን የሚሉትም ሊያብሩ አይችሉም። የቆየው ይቅርና በቅርቡም ኢዴኅቅ፣ ኅብረት፣ ቅንጅት የተባሉት ስብስቦች ጠቃሚ ትምህርትና ተመክሮዎችን የሚለግሱ ናቸው። ስብስቦች ራሳቸው ሲበዙ ወደ ህብረት ጉዞው መደናቀፉን አመልካች ነው። ሙት ለሙት ያለቅሳል እንዲሉ። ስብስቦቹ ራሳቸው ሊስማሙና ሊቀናጁ ካልቻሉ ሌሎችን ሊሻሙ ሊስቡ የሚያደርጉት ጥረት እርስ በርስ በመደነቃቀፍ ፍሬ አልባ ይሆናል።

በህብረትና ድል አቅጣጫ ለመሄድም የሚነሱ አንዳንድ ሀይሎች ሀ ሲሉ ባልሆነ እቅድ ራሳቸውን ቀይሰው ራሳቸውን አደናቅፈው ና መሳለቂያም ሆነው ይገኛሉ። ይህ የስደትና የሽግግር መንግሥት ምስረታ የሚለውን ይመለከታል። የሽግግር መንግስት ወይም ጊዜያዊ መንግስት ሊቋቋም የሚችልበት የትግልና የአብዮት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው። ለምሳሌ በየካቲት 66 ኢሕአፓ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ብሎ ነበር--ስልጣን በመኮንኖች ብቻ እንዳትያዝ። በቬየትናምና አልጄሪያ የተቋቋሙት ጊዜያዊ መንግስታትም የብዙ አመታት ትጥቅ ትግል ውጤቶች ነበሩ። እንዲሁ አንድ ቀን ጠዋት ተነስቶ ያውም ነጻ በወጣ ምድራችን ሳይሆን በባዕድ ሀገር የሽግግር መንግሥት ማቋቋም መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን ሌላ ምንም ውጤት አያስገኝም። በወያኔ አገዛዝ መቃብር ላይ ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት መቋቋም አለበት ሲል አሁንም ኢሕአፓ ያምናል። ትግል ሀ ሳይባል የስደት ወይም የሽግግር መንግሥት እናቋቅም ብሎ መነሳቱ ጋሪውን ከፈረሱ በፊት ማድረግ ነው። በቅርቡ በሊቢያ ያየነውና በሶርያም እያየነው ያለው ከትግል የራቀ ሂደት አይደለም-- በመሰረቱ ግን ይህ የባዕዳንን አሉታዊ ሚናና ድጋፍ የተንተራሰ ነው። የወያኔን አምባሳደር አባሩና "የእኛን ልኡክ" ተቀበሉ ብሎ መነሳት በጥቅሉ ተቃዋሚውን መሳቂያ ያደርገዋል፣ አድርጎታልም። ተደማምረው ተደራርበው --ያውም ይህ መተባባር እንኳን ሳይታይ-- ሚዛን የማይደፉ ቡድኖች የስደት መንግሥት ቢያቋቁሙ በሹመት ሊጣሉ ና ይበልጥ ሊከፋፈሉ ካልሆነ በፖለቲካው መስክ ምንም ፋይዳ አይኖረውም። በቅድሚያ የወይኔን አገዛዝ መታግልና በትግልም መጠናከር መታየት አለበት። ከወያኔ እጅም ስልጣን ልትወጣ ዝግጁ መሆኗ መታየት አለበት። ትግላችን

የተሰበጣጠረና ደካማ ሆኖ ባለበት አንድ ወይም ሁለት ቡድኖች የስደት አሉ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም መነሳት ከባድ ስህተት፤ ትግልን ጎጂና አደናጋሪ ነው። ከመጠምጠም መማር ይቅደም የተባለው በአያሌ ምሑር በሉን ባዮች የተዘነጋ ይመስላል።

ወይኔ ብልጣ ብልጥ ዘረኛና ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን ነው። ድንጉጦችም የተሰበሰቡበት ነው። ብዙሃኑ እንደሚጠሉት ስለሚያውቅም ሁሌም እንደባነነ አለ። ይህ ደግሞ ትግልን ገና ከእንጭጩ ማፈን ማጥፋት (በነሱ አነጋገር ማምከን) በሚለው ያምናሉና ለማንም አይተኙም፤ ማንኛውንም ተቃዋሚ አይንቁም። መደናገሩና መጃጃሉ ያለው ግን በተቃዋሚዎች ጎራ ነው። ይህን ሀቅ አለሽፍንፍን ማቅረቡ የሚጎረብጣቸው አሉ-- ግና ሀቅ ሀቅ ነውና እንደ ሬትም ቢመር መጠጣት--መቀበል አለብን። ወያኔ አፋኝና ጨፍጫፊ አገዛዝ ነው ግን ሙሉ በሙሉ በሀይል ብቻ የሚጠቀም አይደለም። ተቃዋሚዎችን ማደናገርና በብሄረሰብ፤ በሀይማኖት፤ በጥቅም መከፋፋልም ትጥቁ ነው። በመሆኑም ሕዝብን ማደናገርና ተልዕኮና አቅጣጫ ቀይሶ ማንጎድ ማባከን ዋናው ተግባሩ ነው። መላ ኤርትራን ካስረከበና ሀገሪቷን ገንጥሉ ብሎ ለዓለም ከተማጸነና የፈለገውን ካሚላም በኋላ በትንሽ መንደር ባድሜ ከ ወዳጄ ሻዕቢያ ተጣላሁ ብሎ ስንቱን ተላላ አሰልፎ እንዳስጨረሰ ልጅ አልባ የሆኑት ቤተሰቦች ያውቁታል። ወያኔ የሀገርን ድንበር ጠባቂ የመሰላቸውም ከባዕድ ሀገሮችም ገንዘብ ይዘው መጥተው የቧረቁትን የምንረሳው አይደለም። እነዚህ የወያኔ ጀሌዎች እስከዛሬም አጠፉን ይቅርታ ሲሉን አልሰማናቸውም። ወያኔ በኢትዮጵያዊነት ስሜትና በሚጠላት ኢትዮጵያ ሽፋን በዙሪያው በርካታ ጀሌዎችን ሊኮለኩል ቻለ። እስረኛ ይፈታልናልም ያሉት አፍረው ተመለሱ-- በደገፉት ጦርነት ግን ከመቶ ሰላሳ ሺ ያላነስ ዜጋ አለቀ። ሞተም ተብሎ አልተነገረለትም። የወያኔና የሻዕቢያ ግጭት ሰርግ ሊሆን ሲገባው ተዝካር ተብሎ ሊገኝ የሚችለው ሀገርን ጠቃሚ ውጤት መና ቀረ። ዛሬም ስለ ግብጽ "ወረራ" ሊያወሱልን የተነሱት አይነት ያኔም ሻዕቢያ አዲስ አበባን ሲይዝ የታያቸው ጥቂት አልነበሩም።

የ 1080 ኪሎሜትር ዘመቻና ወረራ! በምን ደጀን በምን አቅም? ማን ጠይቆ! ስለ ጦርነትም ግንዛቤ ባዶ ነበር ማለት ይቻላል። ወያኔ ግን በዚህም በዚያም አወናብዶ ማገዶ ጭዳ አገኘ። ሻዕቢያ ወደ ትግራይ ዘልቆ የወያኔን ምርጥ ጦርና ፋብሪካዎችና ተቋሞች ቢያወድም ለኢትዮጵያ በጠቀመ እንጂ የሚጎዳ ባልነበረ ነበር። ወያኔና ኢትዮጵያ ተጻራሪ ናቸውና። ከባድሜ መልስ ወደ መለስ ያሉት በዚያው በባድሜ ቀርተዋል። በወያኔ ቅስቀሳ

ይህ ከሀዲ ቡድን ለሀገር ቆመ ብለው የተወናበዱት ሁሉ ወያኔን አጅበው ሀገርን ጎዱ። ልንጠቅምበት ይቻል የነበረውን የጠላቶች ግጭት አንዱን -- ያውም ኢትዮጵያዊ ያልሆነውን -- በመደገፍ ግጭቱን ልንጠቀምበት አልቻልንም። መጨረሺያውም አላማረም። ወያኔ እቀበለዋለሁ ያለውን የዓለም ፍርድ ቤት ውሳኔ ለሕዝብ ሊሸጥ ሞክሮ ተቀባይ ሲያጣ ተቃወምኩ ያለውን ሕዝብ አልተቀበለም፤ አላመነም። እስከዛሬም ቀውሱ ቀጥሏል።

ወያኔ በባድሜ ሕዝብን ካስፈጀና ሀገርን ለባሰ አደጋ ካጋለጠ በኋላ  በቀድሞው ክሀዲ ጎዳናው ቀጠለ እንጂ ለሕዝብ የሚጠቅም ምንም እርምጃ አልወሰደም። አንድም የፖለቲካ እስረኛ አልፈታም። ከጸረ ኢትዮጵያነቱም ጭራሽ አልቀነሰም። በአሁኑ ወቅት ደግሞ አዲስ ተንኮልና የእልቂት  ሴራ ይዞ ብቅ ብሏል። በቅድሚያ ወያኔ በግብጽና በሱዳን (እንዲሁም በገዳፊ) ተደግፎ ነው ወደ ስልጣን የመጣው። ለስልጣን ሲበቃም ከቀድሞው የግብጽ ፕሬዚዳንት ሙባረክ ጋር ተመሳጥሮና ስምምነትም ተፈራርሞ በጊዜው የኢትዮጵያን ጥቅም ሸጠ ተብሎም ተወግዞ ነበር። ወያኔ ጣና በለስን ከዘረፈና ካፈረሰ በኋላ ሁናቴዎች አስገድደውት  ግድቡ እንዲሰራ ቢደረግም ለወያኔ ቅድሚያው የተከዜ ግድብ መሆኑን ማንም ያውቀዋል-- ወያኔዎች ማለትም መሪዎቹ በነቂስ ኢትዮጵያን ይጠላሉ። ኢትዮጵያና አማራን ተወራራሽ አድርገው ያለች አንጎላቸውን ደፍነዋል። ይባስ ብሎ በወያኔ ዙሪያ የተኮለኮሉ ተለጣፊዎች ሆኑ ራሳቸውን ሕጋዊ ተቃዋሚ ነን የሚሉትም ይህን የወያኔ ጸረ አማራ አቅዋም የሚጋሩ ናቸው። ወያኔ የአባይን ትልቁን ግድብ ሊሰራ የተግደረደረው በሰሜን አፍሪካ የሕዝብ አመጽ ሲስፋፋና በኢትዮጵያም ሊፈነዳ ይችላል ሲባል ነው። የዕቅዱ ውዳቂነትም 4.7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከራሱ የዝርፊያ ካዝና/ሳጥን ሳይሆን በድሀው ሕዝብ ይዋጣል ብሎ ሚቹና ዋሾው አምባገነን መለፈፍ ሲጀምር ነው። ያልታሰበበትና የሚሰራ የሚጨረስ እንቅስቃሴ/ዕቅድ አለመሆኑንም ለማሳየት ይህ በራሱ በቂ ነበር። ይህ የሀገራችንን መሬት ለሱዳን የሰጠ፤ ለህንድ፤ ቻይናና አረቦች የቸበቸበና አሁንም በመሸጥ ላይ ያለ አገዛዝ ቦንድ ብሎ ሊዘርፍና የሕዝብንም  እይታ ወደ ሌላ አቅጣጫ ከመዘወር ሌላ ምንም አላማ አልነበረውም፡ የለውምም። ሰፊ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያውንም አንቅሳቅሶ አባይ ግድብ ወይ ሞት ብለው የሚያቅራሩ---የሚታገሉ ሳይሆን ሕዝብን ለእልቂት የሚያጋልጡ-- ቅጥረኞቹን አሰራጨ። በጥቂት ጊዜም አባይ ግድብ የሚለው ጩኸት ሌላውን ሁሉ ሸፈነው። ይህን የወያኔ ተንኮል አውቀው ያጋለጡና የታገሉትም ቢኖሩም በየ ኤምባሲ ተብዬውና በወያኔ ስብሰባዎች እየተገኙ ለሀገር ጠላት ገንዘብ የለገሱም ነበሩ-- ማንነታቸውንም ሕዝብ ያውቃል፤ ወደፊትም ይጠይቃቸዋል።

የአባይ ተፋሰስ ሀግሮች በአባይ የመጠቀም መብታቸው የሚሻር አለመሆኑ ግልጽ ቢሆንም የአባይ ውሀ የሞት ሽረት ጉዳይ የሆነባት ግብጽም ስግብግብነቷን ቀንሳ አባይን በጋራ ለመጠቀም መዘጋጀት እንዳለባትም ግልጽ ነው። ወያኔ ግን ውዝግቡን አፋፍሞ ወደ ግፍጫ መውሰድ ይፈልጋልና ሀገራዊ ስሜትን ቀስቅሶ ሕዝብን ከጎኑ ለማሰለፍ  በጠብ አጫሪነት እየገሰገሰ ነው። ፉክራውና ሽለላው እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ ግብጽን የምትቋቋምበት አቅም የላትም። ዳግም ዕድሜ ለወያኔ-- ማን ስንት ሚሊዮን ብር የወጣበትን አየር ኃይል አፈረሰ? ማን የመከላከያ ሰራዊት የተባለውንም በጎሳ ጦር ተካው? ማን የሀገሪቷን ምስጢር ለባዕዳንና ለሻእቢያ ሰጠ? ማን ግብጾች ባሕር ዳር ድረስ ዘልቀው እንዲንቀሳቀሱስ ፈቀደ? እንዲሰልሉ--እንዲዘጋጁ ማለት ነው። መልሱ ወያኔ የሚል ነው። የሕዝብን አብዮት ያደናቀፈው የግብጹም ያሁኑ አገዛዝ የራሱ ውስጣዊ የፖለቲካ ችግር ስላለበት የአባይ ውሀ አይቀነስም በሚል ሕዝቡን ወደ ሌላ አቅጣጫ መውሰድ ይፈልጋል። አንዳንዶች በስሜት የሚነዱ እንደሚሉት ግብጽ ኢትዮጵያን በጦር የሚወር ሳይሆን በሱዳንም በኤርትራም ተጠቅሞ ቀላል ባይሆንም በአየር ግቡን መደብደብ የሚችል ነው። ወያኔ ይህን ሊቋቋም አቅም ቀርቶ ፍላጎትም የለውም። ኢትዮጵያም በተምዘግዛጊ ሚሳኤል ወይም ተወንጫፊ ሮኬት የግብጽን አስዋን ግድብ መደብደብ ትችላለች ብለው ራሳቸውን የሚደልሉ ደግሞ ሳይተኙ የሚያልሙ ናቸው። በዚህ ተባለ በዚያ ይህ ያለው ውጥረት ለኢትዮጵያ አይበጃትም። ለነገሩ እስካሁን ያሉት ግድቦች ለኢትዮጵያ የመብራት ሀይል ፍጆታ ከበቂም በላይ ቢሆኑም ዛሬም ኮረንቲ/መብራት በፈረቃ መሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ነው።

ለዚህም ነው አሸር ባሸር ፖለቲካውን ትተን፤ አስመሳይ ሀገር ወዳዶችን ወግዱ ብለን፤ ዋና በሆነው በጸረ ወያኔው ትግል ላይ ማተኮር ያለብን። የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን መንግስት ሲያቋቁም በአባይ ሙሉ በሙሉ የሚጠቀም ይሆናል። እስከዚያው ግን አባይም ቢሞላ ባይሞላ የራሱ ጉዳይ ነው እንደሚባለው ለወያኔ ግድብ የዜጎች ደም ከቶም የሚፈስ አይሆንም ።

ለወያኔ ተንኮልና ሴራ ሰለባ አንሁን!

ጸረ ወያኔው ትግላችን ይፋፋም !!